# ነገ ደሞ ምን ያረገን?

ሌላው ሲነጉድ ወደ ጠፈር፣
ሊፈላሰፍ ሊመራመር፣
እኛ ስንውል ስንናቆር፣
ስንገድል ስናጋድል፣
እንኳን ዜጋ ዛሬ እሚኖር፣
ድንቅነሽስ እንዴት ታፍር?

መሆኑ ነው እድገታችን፣
የሶስት ሺህ ዘመናችን፣
እንደ ፈልስጣ መጨካከን፣
መበላላት እርስ በርሳችን?

ምን እንበለው ይህንን ግፍ?
ልጅ ተነስቶ አያት ሲገርፍ፣
ቋንጃን ቆርጦ ሽቅብ ሲዘልፍ!
ጀርባን ሲሰብር በሰደፍ!

ምን እንበለው ይህን ፍዳ?
እናት ስትጮህ በግፍ ታስራ፣
ጨቅላ ፍትህ በአንቀልባ አዝላ፣
ጨለማ ውስጥ ተወርውራ፣
እህል ውሀ አልቀምስ ብላ፣
ሰቆቃዋን ስትበላ!
በአገሯ ምድር ስታነባ!

በዚያች ምድር በኢትዮጵያ፣
እንኳን ሰው ሊያድግ ሊፋፋ፣
ህሊና እውቀት ሊስፋፋ፣
ደመ-ነፍስም በኖ ጠፋ፣
የሰውም ልጅ ከአውሬ ከፋ!

አስርቱ ቃላት ተጣሰ፣
ቆብ እንደቂጣ ተጎረሰ፣
ክህነት በረብ ረከሰ፣
ሽምግልናውም ኮሰሰ፣
ምነው ቅጣት በኛ ባሰ?

ለባእድ ጌታ አስገብሮን፣
ከባህር ዳር ወደብ ነጥቆን፣
ከመሐልም ፍቅር ነስቶን፣
በጎጥ ጥርሶች አያይዞን፣
እንግዲህማ ምንድን ቀረን?
ነገ ደግሞ ምን ያረገን?

አያት በግፍ አስረገጠን፣
ወላጅ እናትን አስካደን፣
ሽማግሎችን አስቀጠፈን፣
ቅስናንም አስፈረሰን፣
ቆባችንን አስወለቀን፣
ዲግሪን በከርስ አስለወጠን፣
ፍትህ ታንቃ ትሙት አለን፣
የአንገት ማተብ አስቦጨቀን፣
እንግዲህማ ምንድን ቀረን?
ነገ ደሞ ምን ያረገን?

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*
*ታህሳስ ፳፫ ቀን ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም*